

☆ ዴሞክራሲያ ☆

ቅጽ፡2 ቁጥር 18 መስከረም 24 ቀን 1968 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሣን፡፡

በሥልጣን ጥም የሰከሩ፣ ስለ ሰፊው ሕዝብም ሆነ ስለሀገሪቷ ምንም ዓይነት ኃላፊነት የማይሰማቸው ፋሺስት ምርጥ መኩንኖች፣ የሠፊውን ሕዝብ መሠረታውያን ዲሞክራሲያውያን መብቶችን በመግፈፍ፣ ሰላማውያን ሠራተኞችን በመረሸን፡ ሰብአዊ ርሕራሔ የተለየው፣ የሕግ ልጓም የማያውቅ፡ የጭቆና ሥርዓቱ በአገሪቷ ላይ በመዘርጋት ላብ አደሩን ጠቅላላ የሥራ ማቆም አድማ እንዲወስድ አስገድደውታል፡-

ላብ አደሩ ይህንን የሥራ ማቆም አድማ እንዲወስድ የተገደደው ከቀድሞው ብዝበዛ በላይ፣ ለነጻነቱ ለሕይወቱ ምንም ዋስትና የማይሰጥ፣ ምንም ዓይነት አማራጭ የማይተው አምባገነናዊ አመጽ በላዩ ላይ ስለተዘረጋበት መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው፡፡

ላብአደሩ የጠየቃቸው ጥያቄዎች፣ የመላው ሠፊ ሕዝብ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ የጥያቄዎቹ ትክክለኛነት ለማንም ተራማጅ ብቻ ሳይሆን ለማንም ዲሞክራት፣ ለማንም የሠፊውን ሕዝብ ወገን ወጭቆና መረገጥ ለሚጠላ ለማንም ሰዎች አለምክንያት መረሸን የለባቸውም ብሎ ለሚያምን ግልጽ ነው፡ በአጭሩ ጥያቄዎች የሚያከራክሩ አይደሉም፡፡

ነገር ግን ለነዚህ ጥያቄዎች የምርጥ መኩንኖች መንግሥት ምን ዓይነት መልስ ሰጠ? ለጥያቄዎች ከምርጥ መኩንኖች መንግሥት የተሰጠው መልስ፣ አብሪታዊና ፋሺስታዊ ብቻ ሳይሆን ቆትገና ውድቀቱን በህዝብ ደምና አጥንት ለሸፍነን፣ ያለፍና የደቀቀ ህልፈውን በመግኘት ለመለበስ የሚጥር የተስፋ ቢስ መንግሥት መልስ ነው፡፡

ሰፊው ህዝብ ሆይ! የምርጥ መኩንኖች መንግሥት ነኝ የሚለው የወንበዴዎች ቡድን፣ እስከዛሬ ድረስ የተወሰነ መብት ያለህ መሆኑን፣ ሕገና ስርዐት መኖሩንም በቃል ደረጃ ተቀብሎ፣ ሕጉን በመሳለፍ ሲረሽንህ ነበረ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ግን መብቀን መረሸን በኃይል ማስራት ሁሉን በአዋጅ ሕጋዊ አደርገዋለሁ፡፡ እስከዛሬ ድረስ መረሸኑ የግል ሥልጣን ነበረ፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ ግን እያንዳንዱ መለዩ ለቧሽ በግብር በመዘረፍ በመረሸን የወንጀለ ከፋይ እንዲሁን አስገድደዋለሁ፣ ብሎሃል፡፡ መስከረም 19 የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ትርጉሙ ይህ ነው፡፡

ላብ አደር ሆይ! አሁንም የምርጥ መኩንኖች ቡድን ምንም ዓይነት አማራጭ መንገድ አልተወልህም፡ መሠረታውያን መብቶችህን በመጠየቅህ፣ ዳቦና መጠለያ በፈለግህ፣ በመንገዱ አለምክንያት መረሸን የለብኝም በማለትህ፣ ይበልጥ አጨቁንህ አለሁ፣ ይበልጥ አስርህአለሁ፣ ይበልጥ እርሽንህአለሁ፣ በአዋጅ ሁለህንም ወንጀለኛ ብዬሃለሁ፣ ሁላንም መቃብር መረሸን አለብህ ብየሃለሁ፡ ብሎሃል፡፡ በአንድነት ቁም፡፡ ወደፊት ገፋ፣ ታቸንፋለህ፣ ነጻነትህን በትግልህ ታገኛታለህ፣ ደግሞ ማንም ሊነጥቅህ አይችልም፡፡

ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! የላብ አደሩ ጥያቄዎች የያንዳንድህ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ከላብአደሩ ጋር በአንድነት ቁም፡፡ አብረህ ታገል፣ ችግሩን አብረህ ክፈል፣ ድሉንም አብረህ ትካፈላለህ፡፡

የመንግሥት ሠራተኞች! የምርጥ መኩንኖች ቡድን መሣሪያ አትሁኑ፣ ሥራ በማቆም ከላብ አደሩ ጋር ተሰለፉ፡፡

ወጣት ዘማቾችና ተማሪዎች! ስትታገሉለት ለቆያችሁት ለላብአደሩ ድኅነትና ነጻነትና፣ ለሠፊው ሕዝብ መብት ከላብአደሩ ጎን በአንድነት ተሰለፉ፡፡ በቆራጥነት ታገሉ፡፡

[illegible] የኢትዮጵያ ሠራዊት ወታደር ሆይ: በየካቲት 1966 ዓ.ም. የኃይለሥላሴ ፊውዳል ቡርዥ መንግሥት ሥንገዱን በመሠረቱ ጋደኛህ፣ በባለአደሩና በአርሶአደሩ በአጠቃላይ በሠፊው ሕዝብ ላይ አገዛዙ በጣም የቆየበት ጊዜ ለምሬ ነበሁ በሠፊው ሕዝብ ጋር ተነሥተህ:: ከተከፈለበት አርሶ አደር አባት ወገንና በደም ከሚዛመድህ ላብ አደሮችና ተራማጆች [illegible] ህዝባዊ ሥርዐት ለመገበ ለዚህም ለመታገል በቆራጥ በሰምህና በአላማህ ተሰለፍክ [illegible] ደርባ ቆብ አሉ:: ከሰፊው ሕዝብና ካንተ ጭምር [illegible] የቀምበለተገ ላብ አደር አንድነተዘረፍፍ፣ በወገዶቻቸሁ [illegible] አገዶት፡ እስከመጠየቅ ደርሰዋል:: ይህ ሁሉ ለምን [illegible] የሠፊው [illegible] ፍላጎት በመጣሱ፣ የሠፊውን ሕዝብና የአንተንም መብት በመርገጥ አምባገነኖች የገለ [illegible] ለመመስረ ባለቸው ፀረ ሕዝብ አላማ ምክንያት ነው:: ሠፊው የኢትዮጵያ ወታደር፣ [illegible] ምንትና ተራማጅ መኰንኖች የምርጥ መኰንኖች ቡድን የወገደለ ተካሄደ እተሁኑ፣ ከመ[illegible]ቻቸሁ [illegible] አደሮች፣ አርሶ አደሮች፣ ተራማጅ ምሁራን፣ ከዘማቾች፣ ከተገንገሽ ነጋዴዎች፣ ከሠራ[illegible] ወዘተ.. ጉን ቆስልፋችሁ፣ ለነጻነት ለዐድገት፣ ለእኩልነትና ለዲሞክራሲያዊ አንድነት [illegible]ሉ::

የአስቸኳይ ጊዜው አዋጅ ተነስቶ የሠፊው ሕዝብ መሠረታዊያን ዲሞክራሲ[illegible] መብቶች ይ ሰፍኑ፣ ላብአደሮች ያቀረቡት ተከከለኛ ጥያቄዎች ይፈጸሙ:: የታሰሩት መም[illegible]ቶች ወታ[illegible] ሌሎችም ተራማጅ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ::

በመጨረሻም አሁን ያለው የምርጥ መኰንኖች ቡድን እያባባሰው የሄደው የ[illegible] ችግር መጨረሻ መፍትሔ ሊያገኝ የሚችለው የሕዝብ እምነትና ድጋፍ ያለው፣ ከሁሉም [illegible]ው ሕዝብ ወገኖች የተውጣጣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ሲቋቋም መሆኑ ግልጽ ነውና፣ ከተደራጁት የፖለ ፓርቲዎችና ቡድኖች፣ ከኢ.ሠ.አ.ማ.፣ ከገበሬ ማኅበሮች፣ ከመምህራን ማኅበር፣ ከ[illegible] ክራሲያዊ [illegible] ከሚመረጡ የጦር ኃይሎች ወኪሎች እንዲሁም ከሌሎች የሠፊው ሕዝብ ወገኖች የ[illegible] ህዝባዊ ያቀፈ በእነሱ በቻም የተያዘ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም:: በሀገሪቱ ያሉ ተራማጅ [illegible]ቸ፣ ፀረ ፊውዳል፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት፣ ፀረ ብሮክራሲያዊ ካፒታሊና ለዲሞክራሲ ያሉ ፓር[illegible] ሁሉም ለዚህ ግብ የአንድነት ዘገዳቸውን ያነሱ፣ ህብረታቸውንም በጋራ ፕሮግራም፣ በጋራ መሪና በጋራ የትግል ስልት ያስተባብሩ::

ሠፊው ህዝብ ያቸንፋል ::

[illegible]